ሜይ 2018 QuickNotes ቁ. 1

የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ 2019-2020 የትምህርት ዓመት ካለንደር የምላሽ አስተያየት ይፈልጋል።

የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ 2019–2020 ካለንደር ጥናት/ዳሰሳ እያካሄደ ነው። ይህ ዳሰሳ/ጥናት በተለያዩ ቀናት ኃይማኖታዊ እና ኃይማኖታዊ ያልሆኑ በዓላትን ጨምሮ ስለ ት/ቤቶች መዘጋት ጥያቄዎችን ያካትታል። ይህ መረጃ ተተንትኖ እና ተገምግሞ የ2019–2020 የትምህርት ዓመት ካለንደር ለማዳበር እንደግብአት ይጠቅማል። የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከቤተሰብ፣ ከተማሪዎች፣ ከሥራ ባልደረቦች እና ከአጠቃላይ ማህበረሰቡ አስተዋፅኦ እንዲደረግ ይፈልጋል።

ለባለድርሻ አካላት የትምህርት ቤት ካለንደር ጥናት/ዳሰሳ እንዲዳብር ኖቬምበር 14, 2017 ከትምህርት ቦርድ የተሰጠውን ውሳኔ ለመተግበር፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና ሐኖቨር የጥናት ድርጅት (Hanover Research) በመተባበር ሠርተዋል።

ወላጆችና ሞግዚቶች በዳሰሳ ጥናቱ ላይ እንዲሳተፉ እንዴት የጥናት መረቡን ለማግኘት እንደሚችሉ የሚገልጽ መመሪያ በኢ-ሜይል ወይም በፖስታ ካርድ ይደርሳቸዋል። ወላጆች እና ሞግዚቶች እንዴት እና የት ቦታ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን (6 - 12 ክፍሎች) ለዳሰሳ ጥናት ለማግኘት እንደሚችሉ ከተጋበዙበት ካርድ/ኢ-ሜይል ጋር ኢንፎርሜሽኑ ይደርሳቸዋል። ይህ ወላጆችን እና ሞግዚቶችን ለልጆቻቸው የዳሰሳ ጥናቱን ለማመቻቸት ይረዳቸዋል።

የዳሰሳ ጥናቱ ወደ አማርኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኮሪያንኛ፣ ስፓንሽ፣ እና ቬትናምኛ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ሁሉም ተሳታፊዎች በአውታረ መረብ ዳሰሳ ጥናት ወቅት ከእነዚህ ቋንቋዎች አንዱን ለመምረጥ ይችላሉ። በእንግሊዝኛ እና በተተረጎሙ ቋንቋዎች የወረቀት ህትመትም ለማግኘት ይቻላል። በወረቀት ህትመት ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ለ calendarsurvey@mcpsmd.org ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ። የጥናቱ መስኮት የሚዘጋበት ወቅት ሜይ 22/2018 ነው።

በዳሰሳ ጥናቱ ላይ የመሣተፉ ሁኔታ በራስ ፈቃደኝነት ነው፣ እና የሚሰበሰበውም መረጃ በጥንቃቄ እና በሚስጥር ይጠበቃል።

እዚህ ድህረ-ገጽ ላይ የበለጠ መረጃ ይገኛል።
http://www.montgomeryschoolsmd.org/calendar/survey2018/

የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ አዲሱ የአንደኛ ደረጃ ከሪኩለም/ሥርዓተ ትምህርት ምላሽ አስተያየት ይፈልጋል።

የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ አዲሱ የአንደኛ ደረጃ ከሪኩለም ሂደት እና እቅድ ላይ ከወላጆች ምላሽ አስተያየት ለማግኘት ይፈልጋል። የዳሰሳ ጥናቱ ከከሪኩለም 2.0 ጋር ምን ያህል ትውውቅ እንዳላቸውና ምን ያክል ውጤታማ እንደሆነ እንዲመዝኑ ወላጆችን ይጠይቃል።

በተለይም ደግሞ ምላሽ አስተያየት የሚፈልገው ስለ አዲሱ ከሪኩለም/ሥርዓተ ትምህርት ገፅታ፣ ከውጭ የተገዛ ሥርዓተ ትምህርት/ከሪኩለም ጠቀሜታዎች፣ የከሪኩለሙ ውጤቶች ክለሳ በሚደረግበት ወቅት ዲስትሪክቱ ግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ማንኛውም አሳሳቢ ጉዳይ ካለ፣ እና አዲሱ ከሪኩለም በጣም ስኬታማ በሆነ ሁኔታ እንዲናኝ/እንዲተገበር በጣም አስፈላጊ የሆኑ ምክንያቶች፦

የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ Policy IFA, Curriculum/ከሪኩለም የከሪኩለም ይዘት በየአምስት ዓመቱ እንዲጠና ያደርጋል/ይጠይቃል።

የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከሥርዓተ ትምህርት/ከሪኩለም 2.0 ተላቆ ከውጭ ወደ ገበየነው ከሪኩለም ሽግግር ሲያደርግ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡት ምላሽ አስተያየት አስፈላጊ ግምት ይሰጠዋል። ወላጆች እስከ ሜይ 18 ድረስ የምላሽ አስተያየቶቻቸውን እዚህ ለመስጠት ይችላሉ።

ወደ አዲሱ የኤለመንተሪ/አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት/ከሪኩለም ሽግግር የሚካሄደው በ2018 - 2019 በተወሰኑ ት/ቤቶችና በተመረጡ ኮርሶች ይጀምርና በመጪዎቹ ዓመታት እየቀጠለ ይሄዳል።
ተጨማሪ መረጃ

የተማሪዎች መመረቂያ ፕሮግራሞች ሜይ 29 ይጀምራሉ፡-

የ2018 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመመረቂያ ወቅት ማክሰኞ ሜይ 29 እንደሚጀምር እና ዓርብ ጁን 8 እንደሚያልቅ ተወስኗል። በ DAR Constitution Hall የሚካሄደው የምረቃ ስነስርአት በ DAR ትብብር [በ DAR ድር-ጣቢያ] በቀጥታ ይቀርባሉ።

MCPS ወላጆች የሚወዷቸውን የምረቃ ፎቶግራፎች እንዲልኩ ይጋብዛል። ወላጆች የልጃቸውን (የልጆቻቸውን) አጅግ አስደሳች ፎቶ መምረጥና በሚከተለው ኢ-ሜይል pio@mcpsmd.org መላክ አለባቸው። ከነዚህ ፎቶግራፎች ብዙዎቹ በMCPS ድረገጽ ላይ ይለጠፋሉ። ወላጆች እና ተማሪዎች ፎቶዎችን በተጨማሪ በ (hashtag #mcpsgrad) በ Twitter እና በ Facebook ለመላክ ይችላሉ። ከፎቶዎቹ የተወሰኑትን በማህበራዊ ሚድያ ገፆቻችን መልሰን እንለጥፋቸዋለን።

ፎቶግራፎችን ኢሜይል ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ቀላል እርምጃዎች ይከተሉ፡-

- ከሁሉ የላቀውን አግዳሚ ፎቶ ይምረጡ።
- ፎቶውን በ jpeg ፋይል መልክ (ከ 4 MB ያልበለጠ) በኢሜይል ወደ pio@mcpsmd.org ይላኩ።
- የልጅዎን የመጀመሪያ ስም እና የትምህርት ቤት ስም ያሳውቁ። (የመጨረሻ ስም አናትምም።)

ፎቶውን በመስጠት፣ በ MCPS ድረገፅ እንዲታተም ወላጆች ተስማምተዋል ማለት ነው። ጥያቄ ካለዎት Department of Public Information and Web Services በስልክ ቁጥር 240-740-2837 ተገናኙ ወይም በ pio@mcpsmd.org ኢ-ሜይል አድርጉልን።

[የምረቃ ቀኖችና ቦታዎች]

የ 2018 የጌትስበርግ መጽሐፍ ትዕይንት እንዳያመልጥዎት!

የ2018 የጌትስበርግ የመጻህፍት ትዕይንት ቅዳሜ፣ ሜይ 19 የጌትስበርግ ሲቲ አዳራሽ በሚገኝበት ግቢ Gaithersburg City Hall, 31 S. Summit Avenue in Gaithersburg ይካሄዳል።

በትዕይንቱ ላይ እውቅ ደራሲያን እና በሁሉም የእድሜ ክልል ላይ ለሚገኙ ልጆች የሚሆኑ ዝግጅቶች ይቀርባሉ። በርካታ የ MCPS ማህበረሰብ አባላት በፌስቲቫሉ ላይ ምንባብ ያነባሉ/ያቀርባሉ፣ እና ፕሮግራሞች፣ አውደጥናቶች፣ እና በልጆች መንደር ስለምንባብ እና ስነጽሑፍ ፍላጎት የሚያነቃቁ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይቀርባሉ።

ከ 100 በላይ ደራሲዎች እንደሚገኙ በጊዜ ሠሌዳው ላይ ተገልጿል። ከልጆችና ከወጣት ጎልማሶች ደራሲያን መካከል የሚገኙት፡- Sarah Albee, Laura Geringer Bass, Kate Beasley, Kamilla Benko, እና Winifred Conkling ናቸው። ጥቂቶች የስነጽሑፍ

አውደጥናቶች አስቂኝ(ኮሚክ) ታሪኮችን መፍጠር፣ ድንቅ ታሪክ የመናገር ሚስጥር እና እንቆቅልሽ እንዴት እንደሚጻፍ ይዳስሳሉ።

ስለፌስቲቫሉ የበለጠ መረጃ ለማግኘት www.gaithersburgbookfestival.org ይጎብኙ።

Ananya Tadikonda ቀጣይዋ ተማሪ የቦርድ አባል ሆና ተመርጣለች።
Ananya Tadikonda በሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Richard Montgomery High School) ጁኒየር ተማሪ ስትሆን ለ 2018-2019 ተማሪ የትምህርት ቦርድ አባል (SMOB) በመሆን ተመርጣለች። የ Ms. Tadikonda የአገልግሎት ዘመን የሚጀምረው ጁላይ 1/2018 ነው።

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሙሉ ተማሪ የቦርድ አባል (SMOB) ለመምረጥ የሚችሉ ሲሆን 83.6 ፐርሰንት ድምፅ ሰጥተዋል። Ms. Tadikonda ከጠቅላላ ምርጫው ያገኘችው 51 ፐርሰንት ሲሆን የእርሷ ተፎካካሪ Nimah Nayel እንደዚሁ በሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጁንየር 49 ፐርሰንት አግኝታለች።

Ms. Tadikonda በአሁኑ ወቅት የሞንጎመሪ ካውንቲ ሪጅናል (MCR) የተማሪ አስተዳደር አሶስዬሽን ምክትል ፕሬዚደንት በመሆን ታገለግላለች። በተጨማሪም በሜሪላንድ የተማሪዎች ካውንስል የቦርድ ሥራ አስፈጻሚ እና የ MoCo EmpowHER ተባባሪ ፕሬዚደንት በመሆን ታገለግላለች።

ተማሪ የቦርድ አባል (SMOB) የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ድምፅ የሚሰጥ/የምትሰጥ አባል ነው/ናት። ተማሪ የቦርድ አባል (SMOB) የጋራ ድርድር፣ የካፒታል፣ እና የሥራ ማስኬጃ በጀት እና ት/ቤቶች ሲዘጉ፣ እና ዳግመኛ ሲከፈቱ እና በት/ቤቶች ወሰን-ድንበር ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ድምፅ ይሰጣል/ትሰጣለች። SMOB በአሉታዊ የሰው ኃይል እርምጃዎች/ትግባሬዎች ላይ ድምፅ አይሰጥም/አትሰጥም። SMOB አይከፈለውም/አይከፈላትም ነገርግን፣ የ$5,000 የኮሌጅ ስኮላርሺፕ፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሰአቶች፣ እና የክብር-ደረጃ የማህበራዊ ጥናቶች ክሬዲት ይቀበላል/ትቀበላለች።

Ms. Tadikonda የምትተካው ተማሪ የቦርድ አባል፣ የሼርውድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Sherwood High School) ተማሪ Matthew Post የተባለ በሜይ የሚመረቅ ሲንየር ተማሪን ነው።

የበለጠ ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ተማሪ የቦርድ አባል ድረገጽ ይጎብኙ፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ መዝናኛ Move More Montgomery ፌስቲቫል ሜይ 12 ያካሄዳል።

የሞንጎመሪ ካውንቲ መዝናኛ ሦስተኛውን ዓመታዊ Move More Montgomery ፌስቲቫል ቅዳሜ፣ ሜይ 12 ከእኩለ ቀን ጀምሮ እስከ 4፡00 p.m በ Bohrer Park Summit Hall Farm, 506 S. Federick Avenue በ Gaithersburg ይካሄዳል።

Move More Montgomery የተሻለ ጤንነት እና ደህንነትን ለመጠበቅና ለማሻሻል ነዋሪዎች ተነስተው እንዲንቀሳቀሱ ተነሣሣሽነትን ለማበረታታት የተነደፈ ተግባር ነው። ይህ ብዙ ዓይነት እንቅስቃሴዎችን አጠቃሎ የያዘ ፕሮግራም ለሁሉም የካውንቲው ነዋሪዎች ስለ መልካም ጤንነት እና ደህንነት ጠቀሜታ ግንዛቤ ለመስጠት ጥረት ያደርጋል።

Move More Montgomery ፌስቲቫል በመስክ ላይ የሚካሄድ ትእይንት ሲሆን ማህበረሰቡ በመራመድ፣ እንቅስቃሴዎችን እና የአካል ብቃት ሙከራዎችን ማድረግ፣ በንቃት መንቀሳቀስ እና አነስተኛ - ክፍሎች ውስጥ፣ በጋራ የጤንነት ዳስ/መጠለያ፣ ለልጆች የተዘጋጀ ሥፍራ እና እንቅስቃሴዎችን፣ እና Fido Fitness Arena ያካትታል።
ዝናብም ቢሆን ወይም ፀሐይ ዝግጅቱ ይካሄዳል።

የ Move More Montgomery ፌስቲቫል ለMove More Montgomery 100 ማይል ተግዳሮት ጫፍ የሚደረስበት ዝግጅት ነው። በ 100 ቀናት ውስጥ 100 ማይሎችን በመራመድ ወይም በመሮጥ የተጋፈጡ ነዋሪዎች በዝግጅቱ ቦታ ላይ እውቅና ይሰጣቸዋል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ Move More Montgomery Festival ድረገጽ ይጎብኙ ወይም 240-777-6946 ይደውሉ።